# ማለዳ

ድርሻችንን እንወጣ

Maleda

ቅፅ ፩ ቁጥር ፪ መስከረምና ጥቅምት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. Volume 1, Issue 2 ... October 2005

**“... ለህዝብ የምናስተላልፈው መልዕክት የለንም፣ የህዝብን መልዕክት ማዳመጥ ነው ዋናው ጥያቄ ...” ዶ/ር ነገደ ጎበዜ**



**... መሪዎቻችንን ስምንድን ነው እንደአውሬ የምንፈራቸው? ...**

*አርቲስት ታማኝ በየነ*



**የአንድ ቀን መዘዝ ያለዘጠኝ ወር አይመዘዝ**

*ዘነበች ከሲያትል*

**ይህ ቀን አልፎ አድዋን ድል አድርገን አዲስ አበባ እንገባ ይሆን?**

*ከተክለሚካኤል አበበ*



“... ይህ ኢህአዴግ የያዘው አቅጣጫ ለሀገራችን፣ ለኢህአዴጎች ለራሳቸውም የማይበጃቸው መሆኑን ውጭም ያለው ውስጥም ያለው በሰላማዊ መንገድ ኢህአዴግን በአፅንኦት ማሳሰብ ያስፈልጋል ...”

*ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም*

**እኛና እህል**

*ያሬድ ከንፈ ከስዊድን*

# ማለዳ

ማለዳ ቅፅ ፩ ቁጥር ፪
MALEDA VOLUME 1, ISSUE 2
መስከረምና ጥቅምት
፲፱፻፺፰ ዓ.ም.
OCTOBER 2005

## ቃለምልልስ



“... አሁን ህዝባችን ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሷል፣ ከዳር እስከዳር ይህን ምርጫ ይህ መንግስት አጭበርብሮ ነው ያሸነፈው፣ ተሰውቼ፣ ታግዬ ያገኘሁትን ድል ተቀምቻለሁ የሚል በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ነው ...
“ምርጫ የድል አጥቢያ አርበኛ ነው”
ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

“... ደህና ይህ ስም ማጥፋት እኮ ትግል ማጥፋት ማለት ነው። ከእኛ ልምድ በስም ማጥፋት ይጀመርና አቋምን ማንቋሸሽ፣ በሰው ላይ በግለሰብ ላይ ማተኮር፣ ... ይሄ የኢህአዴግ ታክቲክ (አካሄድ) ነው። እናም ትግልን ማጥፋት ነው እንጂ ምንም ልማት የሚያመጣ ነገር አይደለም። ስለዚህ አንደኛ ነገር፣ እንደዚህ የሚሰነዝሩ ሰዎች በግድ መቆጠብ አለባቸው። በተለይ አሁን ባለንበት ደረጃ። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ስማቸው ይጠፋል የተባሉ ሰዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ንቀው መተው ነው ያለባቸው። አሁን ከምርጫው ወዲህ በግለሰብ ደረጃ እንደኔ የሚወረድበት ያለ ሰው አይመስለኝም። በኢህአዴግ በኩል በተቃዋሚ በኩል ሳይሆን በኢህአዴግ በኩል። ግን ዝም ብዬ ነው የምተወው። ...” ... **በገፅ ፯**

→ p6

## ዛሬ



“... በተጨማሪ ደግሞ መንግሥት ራሱ ሕገ-መንግሥቱን ጥሷል። መንግሥት ሕገ-መንግሥቱን በሚጥስበት ጊዜ ለህዝቡ ምን አይነት ምሳሌ ነው የሚሆነው? ህዝቡን ራሱ “ሕገ-ወጥ ሁን፣ ሕግ አልባ ሁን” ማለት ነው። ስለዚህ የተለያየ የሕገ-መንግሥቱ አንቀፆች እንደተጣሱ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም። ...”
ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማሪያም ... **በገፅ ፱**

## ጥበብ



” ... የምወደውን ነገር በሙሉ አጥቼ ነው የመጣሁት። ... እንግዲህ ደስታ በምን ይለካል ነው? ደስታ በምትነዳው መኪና፣ በምታገኘው ገንዘብ ልክ፣ በምትኖርበት ቤት ጽዳት አይደለም የሚለካው። ደስታ አይለካም አይገዛም። ያን ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረኝን ደስታ አላገኘውም ...

አርቲስት ታማኝ በየነ **በገፅ ፲፫**

## ግልገል ማውጫ


| | |
|---|---|
| መልዕክቶቻችሁ | ፪ |
| የማለዳ መልዕክት | ፫ |
| ሐገር እንዴት ሰነበተች | ፬ |
| ቃለምልልስ | ፯ |
| ዛሬ | ፱ |
| የማለዳ ስንቅ | ፲፩ |
| የኛ ሰው በስደት | ፲፫ |
| ጥበብ | ፲፭ |
| ዓለም አቀፍ | ፲፯ |
| የግጥም መድብል | ፳ |
| አጫጭር ዜናዎች | ፳፩ |
| እንተዋወቅ | ፳፪ |
| ሹክ ልበልዎ | ፳፫ |
| ከ/ለ-አገር ቤት | ፳፬ |
| ትዝብት | ፳፯ |

# ቃለምልልስ

## (ከገፅ ፳ የዞረ)

ባሉት እንዲሆኑ ነው። ያሉት ምንድን ነው ተጭበርብሯል ነው። ስለዚህ ተቀበሉ አትበሉን፣ እኛ ሃሳብ አቅርበናል። ይህ ሃሳብ በአጠቃላይ ኅብረተሰባችን አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት፣ ማለት የህዝብ ድምፅ በደንብ ተከብሮ የሚወጣበት፣ ... የህዝብ ድምፅ በደንብ ከተከበረ ደግሞ ተቃዋሚዎች አሸናፊ ሆነው ይወጣሉ። ይህ ብቻ ሳይሆን እኛ ሁላችንም አሸናፊ ሆነን የምንወጣበት የሽግግር ዘመን እንከፈት ብለናል። ኢህአዴግን ጥግ ላይ ወጥረን አንይዝም። ሁለት ዓመት፣ ሁለት ዓመት ተኩል የሽግግር ዘመን ስለሚያስፈልገን ህዝብ በሆደ ሠፊነት ከድሉ ለኢህአዴግ መሪዎችም ለማካፈል ዝግጁ ነው - ለሁለት ዓመት። እና ይህንን ግፊት የምናደርገው እኛ አንደኛ አንድ ዓይነት አቋም እንዲኖራቸው ነው። ከእሉት ጋር አመክኖአዊ እንዲሆኑ ነው። ተጭበርብሯል ካሉ ተቀበሉ ማለት የለባቸውም። ሁለተኛ መፍትሔ በሚሉበት ጊዜ እኛ ያቀረብነው መፍትሔ አለ። ያንን ተቀብለው፣ ማለት ለሁለት፣ ለሁለት ዓመት ተኩል የብሔራዊ አንድነት መንግሥት ተቋቁሞ፣ የዴሞክራሲያዊ ኮሚሽን ተቋቁሞ፣ የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን ተቋቁሞ ኅብረተሰባችን ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሰናዳ የሚደረገውን ትግል ደግፉ እንላለን። በአቋማቸው ከፀኑና ሃሳባቸውን ካልቀየሩ፣ ተቃዋሚዎች ከሚያራምዱት አቋም ሌላ ምንም ሲያራምዱ አይታየኝም። እና ለዚህ ነው የምንሰራውም። መስከረም 22 ኅብረተሰቡ በአውሮፓ ደረጃ የተቀነባበረ ኅብረ-ህዝብ በአውሮፓ ፓርላሜንትና ኮሚሽኖች ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ይደረጋል። የምናቀርበውም ጥያቄ ይሄ ነው። "በአቋማችሁ ፅኑ! አመክንዮ ይኑራችሁ! ... እራሳችሁ ካላችሁት ነገር ጋር የሚጋጭ ነገር አትበሉ! ተጭበርብሯል ብላችኋል!" ብለን አቋማችንን እንደረድራለን። በዚህ ፀንተው እንደሚቆሙ ተስፋ እናደርጋለን። አለበለዚያ በእውነቱ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ተስፋ መቁረጥ ያስፈልጋል ማለት ነው።

*__ማለዳ፦__ ለኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ሀገር ውስጥ ያለውን በዚህ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ምን ዓይነት መልዕክት ሊያስተላልፉለት ይፈልጋሉ? ድምፁ በመታፈኑ ካደረበት ቁጣ በመነሳትም ሆነ አገዛዙ በስልጣን ከቀጠለ በበቀል ስሜት ግፍ ሊያወርድብኝ ይችላል በሚል ስጋት ሊያነሳ የሚችለውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ በምን መልክ መግራትና በሀገሪቱ የከፋ ትርምስ ሳይሆን ለሀገሪቱ ለውጥ ሊያመጣ በሚችል መልኩ መቃኘት እንደሚገባው ይመክሩታል?*

__ዶ/ር ነጋዶ፦__ ደህና! አሁን ለህዝብ የምናስተላልፈው መልዕክት እምብዛም የለንም። የህዝቡን መልዕክት ማዳመጥ ነው ዋናው ጥያቄ። ህዝባችን ማንኛችንም - እኛም፣ ኢህአዴግም፣ ዓለም አቀፍ ኮምዩኒቲውም ከጠበቅነው በላይ ብስለት፣ ብልህነት፣ ጨዋነት፣ የሰከነ ትግል አካሂዷል። መስዋዕትነት እየከፈለ ሳይቆጣ ምንም ሳይል ድል አግኝቷል። እና እኛ አሁን ለህዝባችን የምናስተላልፈው ምንም መልዕክት የለንም። ከኛ ያው የሚጠበቀውም፣ እኛ ሰምተንሃል፣ አድምጠንሃል - የምትለውን በልብ ትርታ ደረጃ ሳይሆን ሳንቃው እስኪሰነጠቅ ነው የሚጮኸው ያንን ሰምተናል። እኛ ነን መልዕክቱን መቀበል ያለብን። እንግዲህ መልዕክት ማስተላለፍ ካስፈለገ ትግሉ በሰከነ መልክ እንዲቀጥል፣ በጨዋነት እንዲቀጥል ከተንኳሾች፣ ከኢህአዴግ ተንኳሾች፣ ... ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጣ ከኢህአዴግ ተንኳሾች እንዲጠነቀቅ። እነሱን ተስፋ እንዲያስቆርጥ። ማለት እነሱም ለማዝረክረክ ነው የሚፈልጉት እና ከዚህ ተጠንቅቆ፣ ከማንኛውም ሕገ-ወጥ ድርጊት ተጠንቅቆ፣ በሕገ-ወጥ ድርጊት የሚሰማሩ ሰዎች ካሉ እነሱን እየያዘ ለኢህአዴግ ፖሊስ እያስረከበ ትግሉን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲቀጥል ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ በቁጣ ገንፍሎ እንዳይወጣ። ለዚህም ነው መስከረም 22 ሠልፍ እናካሂዳለን፣ ለዚያ ተዘጋጅ ያልነው። ከዚያ በፊት ግን አንዳንድ ተንኳሾች ሠልፍ ውጣ ቢሉት እንዳይወጣ፣ ቀኑ ተወስኗል። በዚያን ቀን በዚህ ስብሰባ ላይ ደግሞ ስለቀጣዩ ትግል ስትራቴጂያዊ ይሆንለታል። በዚያ መሠረት እንዲንቀሳቀስ በጨዋነት እስከአሁን በታየው ጨዋነት በሰከነ መልክ ትግሉ እንዲቀጥል ከአወናባጆች፣ ከኢህአዴግ ሰርጎ-ገቦች፣ ከትንኮሳዎች እራሱን እንዲጠብቅ፣ አለበለዚያ ነገሮች ሊበላሹ ስለሚችሉ እራሱን ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ ነው የምንለው ምክር ካስፈለገ። ነገር ግን፣ ለህዝባችን ምክር የሚያስፈልግ አይመስለኝም። በእውነት! በበቂ ጨዋ ነው። በበቂ ሕግ አክባሪ ነው። ስለዚህ በዚህ በኩል እኔ ብዙ ችግር አይታየኝም። ግን ከሰርጎ-ገቦች መጠንቀቅ ይኖርበታል።

> "... በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ወገን የሄድን እንደሆነ አንድ ትልቅ ችግር ምንድን ነው፣ "ኢህአዴግ ሽንፈትን በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ አይደለም፣ ተቃዋሚዎችም አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ ብቁ አይደሉም" የሚል አቋም አለ ..."

*__ማለዳ፦__ ይህንን ሊከተል የሚችለውን ህዝባዊ ተቃውሞ በተመለከተ የተቃዋሚዎች ሚና ምን መሆን ይገባዋል ይላሉ? የዛሬ ሁለት ወር አካባቢ ለ'ኢትኦጵ' ጋዜጣ እንደገለፁት ከኢህአዴግ ጫጫታ ይልቅ የተቃዋሚዎች ዝምታ ይበልጥ ያስጨንቀኛል ብለው ነበር። አሁንስ አያንዳንዱ ዕለት በተለይም በተቃዋሚ ጎራ አንዳች ሚዛን የሚደፋ እንቅስቃሴ በምትጠይቅበት ፈታኝ ወቅት ላይ እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ጊዜው ከሚጠይቀው ታላቅ ኃላፊነት አንፃር አጥጋቢ ትርጉም የሚያሳዩ ሆነው አግኝተዋቸዋል ወይስ ይበልጥ እያስጨነቀዎት ነው ያለው?*

__ዶ/ር ነጋዶ፦__ እያስጨነቀኝ ነው - በእውነቱ! ይህ ሃሳብ እንኳን ከመጣ ወደ 15 ቀን ሆኖታል። እንግዲህ የሀገር አቀፉ ጉባዔ የሚባለው በዚህ ላይ ያለው እንቅስቃሴ ያንን ያህል ፍጥነት የለውም። ተስፋ አለኝ በሚቀጥሉት 15 ቀናት ወሳኝ የሆነና የሚለይበት ሁኔታ ይፈጠራል። እና ሲቪል ማኅበረሰቡ፣ ሌሎች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ይህ ስብሰባ እንዲደረግ በያለበት ግፊት ማድረግ አለባቸው። ትግላቸውን የሚጎትቱ ሰዎች ካሉ በርቱ ታገሉ! ሌላ የመፍትሔ ሃሳብ ካላቸው ደግሞ በርቱ አምጡ እያሉ ማበረታታት ያስፈልጋል። እና ከኅብረተሰቡ፣ ከዴሞክራቶች፣ ከሀገር ወዳድ ኃይሎች ግፊት ያስፈልጋል። የፖለቲካ ድርጅቶችን 'ይህ ዝግጅት ምን ደረሰ? አላችሁበት ወይ?' ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ከሲቪል ማኅበረሰብ መምህራን ማኅበርም፣ ጋዜጠኞች ማኅበርም፣ የአርበኞች ማኅበርም ተጋብዘዋል። ቅድም ዘርዝሬአለሁ። እነዚህ ሁሉ ተጋብዘዋል። እነዚህ ሁሉ ባሉበት 'ይህ እንትን ምን ደረሰ? ወይ እንስማማለን ወይ አንስማማም በሉ' እያሉ እንዲጠይቁ ያስፈልጋል ማለቴ ነው። ብዙ ጊዜ ስለሌለ ግን በሚመጡት ቀናት፣ በሚመጣው ሣምንት ብዙ ነገሮች ይጠራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እስከ አሁን ግን ትንሽ የፈዘዘ ሁኔታ ስለሚታየኝ ትንሽ ጭንቀት አለብኝ።

*__ማለዳ፦__ የተቃዋሚዎች አገር አቀፍ ጉባዔ መጥራትም ሆነ ሽዶ ኀሽርንመንት ማቋቋም ያለውን አስፈላጊነት በተመለከተ በርስዎ በኩል የቀረቡ በሳል አስተያየቶች ነበሩ። እስከ እነዚህን ፍሬ ሃሳቦች በተመለከተ ለአንባቢያቻችን*

> *... ከዛሬ 30 ዓመት ወዲህ ዛሬ ሀገራችን ይበልጥ ድሃ ነች። ህዝባችን ይበልጥ ይበልጥ ድሃና ጎስቋላ ነው ...*

*ያካፍሏቸው። ርዕሰ ጉዳዮቹስ በሕብረቱና በቅንጅቱ በኩል ምን ያህል ተቀባይነት አግኝተዋል ይላሉ? ከሆነስ ምን የተደረገ እንቅስቃሴ አለ?*

__ዶ/ር ነገደ፡-__ ይሄ ሃሳብ የቀረበው ከምርጫው በፊት ነው። ትገዛ ይላችሁ እንደሆን መጽሐፌ ላይ የቀረበው፤ ከዚህ በፊትም ለህዝብ ባቀረብነው ሃሳብ ትግላችን ተዓማኒነት እንዲኖረው፣ ህዝብም እዚህ ምርጫ ውስጥ በሙሉ ልብ እንዲገባ ተቃዋሚዎች ካሸነፉ በኋላ በስልጣን ሲሾሙ አገሪቱን ትርምስ ውስጥ ይከቷታል የሚለውን ስጋት ለማብረድ፣ ይህን ይህን ሁሉ ሁኔታ ለመቋቋምና ህዝባችን በሙሉ ልብ ብናሸንፍ ይህ ነው ፖሊሲያችን፣ ይህ ነው የሽግግር ዘመን፣ ይህን ይህን እንሠራለን፣ ይህንን የሚሠሩ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትራችን እገሌ ነው፣ የፋይናንስ ሚኒስትራችን እገሌ ነው ብለን ከወዲሁ አዘጋጅተን ለትግሉ ትልቅ እርምጃ ይሆናል የሚል ሃሳብ ነበረ በኛ በኩል የቀረበው።

በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ወገን የሄድን እንደሆነ አንድ ትልቅ ችግር ምንድን ነው፤ **"ኢህአዴግ ሽንፈትን በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ አይደለም፤ ተቃዋሚዎችም አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ ብቁ አይደሉም"** የሚል አቋም አለ። ለዚህም ነው በኢህአዴግ አንፃር መወላወል የሚያሳዩት። ማለት በኃይል ከማውገዝ የሚቆጠቡት። መጀመሪያ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ፤ ቀጥሎ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡ ዘንድ ተዓማኒነት ለማግኘት "ይኸው እንዲህ አይነት ፖሊሲ አለን፣ እንዲህ አይነት ካቢኔ አለን፣ አገሪቱ ወደ አለመረጋጋት አትሄድም" የሚለውን ነገር ለማሰማት የቀረበ ሃሳብ ነበር። ይህ ሃሳብ እንኳን ብዙ ክርክር አልተካሄደበትም። እና አሁንም ቢሆን ሌላ ሌላ አጣዳፊ ተግባሮች አሉብንና እናነሳውም እንጂ፤ ይህንን የሚያነሱ ሰዎች ካሉ ይሄ ይሄ አጀንዳ ውስጥ ከገባ ከምናቀርበው ሃሳብ ጋር ምንም ተቃርኖ የለውም።

ኢህአዴግ እምቢ የሚል ከሆነ እኛ በዚህ እንቀጥላለን። ይኸው እንደዚህ ካቢኔት አለን ብለን መቀጠል እንችላለን፤ ምንም ችግር የለውም። ግን እስኪ መጀመሪያ ይህ ስብሰባ ይጠራ። በዚህ ስብሰባ ሃሳብ እንስማማ። የማይስማሙ ሰዎች ካሉ ደግሞ ሌላ ምንድን ነው የሚያቀርቡት መፍትሔ? አሁን እንደምናየው በቅንጅቱ በኩል ህዝብ እየተወያየ ነው ይባላል። በያለበት ፓርላማንት አትግቡ ነው የሚለው። ሪፖርቱ ሲቀርብ ህዝብ በሁለት ተከፍሏል ነው የምንሰማው። በቅንጅት አመራር ሰዎች የምንሰማው ግማሹ ግቡ ይላል ግማሹ አትግቡ ይለናል ነው። እሱን እንግዲህ አይታችኋል ሪፖርቱን። እንደሱ አይደለም እውነቱ። እውነቱ ያለው ዘጠና በመቶው መግባት የለባችሁም ነው የሚለው ህዝቡ። እና ይህን ህዝብ በተበታተነ ሁኔታ ማወያየቱ በቂ አይደለም። የህዝብ ተወካዮች ተሰብስበው ውይይቱ መቋጠር አለበት ነው እንጂ፤ ይኸ ህዝብ በያለበት የሚደረግ ውይይት ይህንን ጉባዔ አይተካውም የሚል እምነት አለ። ይህ የማያልቀውም ሃሳብ ሰዎች ካቀረቡት የማይታይበት ምክንያት የለም። ዋናው የሚወያይበት የህዝብን ድል ለማስከበር ምን አይነት ትግል እናካሂድ በሚለው ላይ ነው። እና በዛ ላይ መፍትሔ የሚያቀርብ ኃይል ካለ ሊቀርብ ይችላል ማለቴ ነው።

***ማለዳ፡-*** *በቅርቡ የሕብረቱ አባል ድርጅቶች በሰሜን አሜሪካ ተሰባስባችሁ ጉባዔ ማካሄዳችሁ ተዘግቧል። እስኪ ስለዚህ ጉባዔና አሳድሯል ስለሚሉት ፋይዳ ይግለጹልን?*

__ዶ/ር ነገደ፡-__ የጉባዔው ትልቁ ፋይዳ ውኅርንብር ሊኑሩ የሚችሉና አንዳንድ ጥራት የሚያስፈልጋቸውን የአቋም ጥያቄዎች በደንብ አድርጎ ፍርጥርጥ አድርጎ ግልፅ አድርጓል። እንግዲህ 14 ድርጅቶች ከሀገር ቤትም ከውጭም ተሰብስበን፣ አንደኛ የምርጫ ሂደቱ ተጭበርብሯል፣ ፍርድ ቤት መሄድ ከአሁን ወዲያ ዋጋ የለውምና አንቀበለው፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አይቀበለውም። እኛም አንቀበለውም። ሁለተኛ ይህንን ካልን ዘንዳ ምንድን ነው መፍትሔው፤ 1ኛ) ጠቅላላ የምርጫው ሂደት በዚህ በምርጫ ቦርድ ሳይሆን በገለልተኛ አካል ይገምገም፣ ይጣራ። 2ኛ) የህዝብ ድምፅ ሳይሰረቅ እንግዲህ የቀረበው መፍትሔ ማለቴ ነው የሽግግር መንግሥት በፕሮግራም የነበረ ስለሆነ፣ ሁለት - ሁለት ዓመት ተኩል ያህል የሚቆይና ኢህአዴግንም ያካተተ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚል በፊት ሲንሸራሸር የነበረውን ሃሳብ ነው ጉባዔው ያፀደቀው። ይህ ነው እንግዲህ። 1ኛ አንቀበልም፣ 2ኛ) ይህንን አማራጭ ሃሳብ እናቀርባለን፣ 3ኛ የዚህ ጉባዔ አዲሱ ውሳኔ ይህንን ገንቢ ሃሳብ ኢህአዴግ የማይቀበል ከሆነ ምን አይነት ትግል ነው የምናካሂደው? በሚለው ላይ ሠፊ የሆነ ውይይት ነው የተካሄደው።

ሠላማዊ ትግል ማለት ብቻ አይበቃም። በሕጋዊ ትግል የሆነ ማለት ብቻ አይበቃም። ምን አይነት መልክ እንዳለው ቀኑን ወስነን መስከረም ሃያ፣ ሃያ አንድ አገር አቀፍ ጉባዔ ማካሄድ። በዚህ ጉባዔ የሚጋበዙ ድርጅቶች በሰነዳችን ወጥተዋል፣ ወደ 31 ናቸው። የአገር ሽማግሌዎችም የሚባሉትም ተዘርዝረዋል። ታላላቅ ግለሰቦች ከየዘኑ የሚታወቁ፣ ከየዘኑ ታዋቂ ነጋዴ ተወካዮች፣ የመምህራን ተወካዮች፣ የኢትዮጵያ ኮሌጆችና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፣ ከንግድ ምክር ቤት አባላት፣ የአርበኞች ማኅበር ኮሚቴዎች፣ ... እንዲህ እያልን በሙሉ ተዘርዝረዋል። የእነዚህ ተወካዮች ሁሉ መጥተው የጋራ ስትራቴጂ ይነድፋሉ። እኛ ብቻችንን እንንደፈው አላልንም። እዛው የችግር አፈታቱ ላይ ከዋና ዋናዎቹ ተሳታፊዎች ማለትም ከቅንጅት፣ ከመምህራን ማኅበር፣ ከፕሬስ ማኅበር፣ ... ከመሳሰሉት የተውጣጣ ነገሩን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚያካሂድ አንድ አዘጋጅ ግብረኃይል እንዲቋቋም የሚል ውሳኔ ተወስኗል።

ትልቁ ነገር ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት ለማራመድ የሚችል ውሳኔ ተወስዷል። እናም በጣም በጣም ስኬታማ ጉባዔ ነበር ብዬ ነው የማምነው።

***ማለዳ፡-*** *አንዳንድ በውጭ በስደት የሚገኙ ኢትዮጵያውያኖችም ሆኑ የፖለቲካ ሰዎች በሀገር ቤት የሚገኙ ፖለቲከኞች ላይ ከፍተኛ የሆነ ትችት፣ ስም ማጥፋትና ዘለፋዎች ሲሰነዘሩ ይሰማል። ይህንን እንዴት ያዩታል? ትግሉስ በጠራ ሁኔታ እንዲቀጥል ይህ አጉል ትችትና ዘለፋ ቀርቶ በመልካም ሁኔታ እንዲቀጥል የርስዎ ምክር ምንድን ነው?*

__ዶ/ር ነገደ፡-__ ደህና! ይህ ስም ማጥፋት እኮ ትግል ማጥፋት ማለት ነው። ከእኛ ልምድ በስም ማጥፋት ይጀመርና አቋምን ማንቋሸሽ፣ በሰው ላይ በግለሰብ ላይ ማተኮር፣ ... ይሄ የኢህአዴግ ታክቲክ (አካሄድ) ነው። እናም ትግልን ማጥፋት ነው እንጂ ምንም ልማት የሚያመጣ ነገር አይደለም። ስለዚህ አንደኛ ነገር፣

> *... የዚህ ጉባዔ አዲሱ ውሳኔ ይህንን ገንቢ ሃሳብ ኢህአዴግ የማይቀበል ከሆነ ምን አይነት ትግል ነው የምናካሂደው? በሚለው ላይ ሠፊ የሆነ ውይይት ነው የተካሄደው። ... ሠላማዊ ትግል ማለት ብቻ አይበቃም። በሕጋዊ ትግል የሆነ ማለት ብቻ አይበቃም ...*

እንደዚህ የሚያደርጉ ሰዎች በግድ ከድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው። በተለይ አሁን ባለንበት ወቅት። ሁለተኛ ነገር ደግሞ ስማቸው ይጠፋል የተባሉ ሰዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው ንቀው መተው ነው ያለባቸው። አሁን ከምርጫው ወዲህ በግለሰብ ደረጃ እንደኔ የሚወረድበት ያለ ሰው አይመስለኝም - በኢህአዴግ በኩል፤ በተቃዋሚ በኩል ሳይሆን በኢህአዴግ በኩል። ግን ዝም ብዬ ነው የምተወው። እና ይሄ በተቃዋሚዎቹም ሰፈር ስም ማጥፋት ላይ የተሰማሩ ኃይሎች ካሉ አንደኛ እነሱን ተስፋ ማስቆረጥ ጠቃሚ ነው። ሁለተኛ ግን ዋናው ትግሉ ወደ ጥፋት እንዳይሄድ ከተፈለገ እነዚህ የስም ማጥፋት ጥቃት የሆኑ ሰዎች በእውነት ንቀው ማለፍ አለባቸው። እንደማይረባ ነገር አድርገው ማየት አለባቸው። ችላ ብለው በዓላማቸው ፀንተው መቀጠል አለባቸው። እኛ በመንግሥታት ደረጃ ያለ ስም ማጥፋትን እየተቋቋምን ነው የምንታገለው። በግለሰቦችና በድርጅቶች ደረጃ የሚካሄድን ስም ማጥፋት መቋቋም ብዙ አስቸጋሪ አይመስለኝም። ግን ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶችም ይህንን ተስፋ ለማስቆረጥ መጣር አለባቸው። እነዛም ማዳመጥ የለባቸውም፤ ችላ ብለው ንቀው መተው ነው ነው የምለው።

**ማለዳ፦** *ዶ/ር ነገደ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የጎላ ሚና እንዳለዎት ይታወቃል። በተለይ ደግሞ በቅርቡ ባሣተሙት መጽሐፍዎና ምርጫ/97ትን በተመለከተ በተከታታይ በሰጡዋቸው በሳል አስተያየቶችና ቃለምልልሶች ሳቢያ ከኢህአዴግ በኩል ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያለማቋረጥ የተደረገብዎት ሲሆን፤ ከህዝቡ በኩል ደግሞ ከፍተኛ ተሰሚነት እንዳተረፈልዎት ይታመናል። እርስዎስ በግልዎ የሚሰማዎት ምንድን ነው? አስተዋፅኦዎ ውጤት እያሳየ ነው ይላሉ? ወይስ ይበጃል ያሏቸው ሃሳቦችን ተግባራዊ ለማድረግ አልሳካ እያለ ጭንቀትና ቁጭት እያሳደረብዎት ነው?*

**ዶ/ር ነገደ፦** እስከ አሁን ድረስ ይበጃል ብዬ ያቀረብኳቸው ሃሳቦች ዋናው መጀመሪያው ህዝቡ በሙሉ ልብ እዚህ ምርጫ ውስጥ እንዲገባ፤ ኢህአዴግ በዓለም አቀፉ ኮምዩኒቲም፤ በኢትዮጵያ ህዝብ ፊትም ሲያጭበረብር ይያዛል፤ እንግባበት ብዩ ለሁለት ዓመት ከመኢሶን ጋር ሆነን በኃይል የታገልንበት ነው። እሱ ሰርቷል። ከጠበቅነው በላይ። አሁን ያለንበት የዴሞክራሲያዊ ትግል ነው። ለዚህ ደግሞ ያቀረብናቸው አገር አቀፍ ጉባዔ የሚባለው መጽሐፉ ላይ ያልነው የሲቪል ኮሚኒቲውን በአንድ ላይ ሰብስበን ከተን በዚህ ነው የምንቀጥለው። ምክንያቱም ከተጭበረበረ በኋላ የሚደረገው ትግል የምርጫ ትግል አይደለም፤ የዲሞክራታይዜሽን ነው። ማለት በፊት ያነሳናቸውን ነው፤ የመገናኛ ብዙኀኑ ለሁሉም በጋራ ይሁኑ፤ ምርጫ ቦርዱ ሁሉም የሚስማሙበት ይሁን። እንዲህ እንዲህ አይነቶቹን የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ይዘን ነው የምንታገለው። ምርጫ ይደገም እንኳ ቢባል፤ በዛው ምርጫ ቦርድ፤ በዛው የማስታወቂያ ሚኒስትር፤ በዛው የመገናኛ ብዙኀን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆነው አይደለም። ኅብረተሰቡ ዴሞክራቲክ ሆኖ ነው። መጽሐፌ ላይ ልብ ብላችሁት እንደሁ "ምርጫ የድል አጥቢያ አርበኛ ነው" ይላል። የምለው በዴሞክራሲያዊ ትግል ልንሠራበት

> … ያለፈው ክፍለ ዘመን የባከነ ብኩን ክፍለ ዘመን ነው፤ ፊት ኃይል የሆነ የሚል ነው ያለኝ አመለካከት …

እንችላለን። በዛ ሳቢያ የሚቀሰቀሰውን ኃይል ይዘን ለመቀጠል ነው። አሁን ያለንበት ምዕራፍ ይሄን የተነሳውን ህዝብ፤ በእርግጥ ነፃ ምርጫ፤ በእርግጥ ዴሞክራቲክ በሆነ ኅብረተሰብ ውስጥ እንዲካሄድ ለማድረግ፤ ትግሉን እንዲገፋ እናበረታታለን። በዚህ በዚህ ያቀረብኳቸው ሃሳቦች መሳካታቸው ደስ ይለኛል።

ሌላው የስድቡ ውርጅብኝ ነው። 'የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም' የሚባል ነገር አለ። ለሠላሳ ዓመት ሲወረድብኝ ነበር። ምንም ከዓላማየ ወደኋላ አይለኝም። ዋናው ግን ይበልጥ ደስ የሚለኝ የኢትዮጵያ ህዝብ እኔን ከማድነቅ ይልቅ፤ ተቃዋሚዎችም እኔን ከማድነቅ ይልቅ ሀሳቤ በሥራ ላይ ቢውልልኝ በጣም ደስ ይለኛል። እሱ ነው ዋናው ነገር። እስካሁን ድረስም ደስተኛ ነኝ። በእውነቱ የምንለው እየተሳካ ነው። አሁን ወሳኝ ሰዓት ላይ ደርሰናል። በሚመጡት 15 ቀናትና አንድ ወር ሁለት ወር ውስጥ ይህ ነገር ወይ ያልፋል። "ወይም ሥራ ወይም ተሰበር" የሚባለው ነገር አለ አይደለም?! … አሁን በጭንቀት ላይ ነው ያለሁት።

**ማለዳ፦** *ከ30 ዓመት በላይ በትግል ላይ መቆየት ቀላል ነገር አይደለም። እንደው ጥያቄዬን በጣም ግላዊ ሳደርገውና ይህን ያህል ጊዜ መታገል አይታክትም? "አሁንስ በቃኝ እንዳሻው ይሁን!" በሚል ተስፋዎን የሚፈታተን ሁኔታ የተፈጠረበት ጊዜ የለም?*

**ዶ/ር ነገደ፦** ይኖራል። እንዲህ አይነት ጊዜ ይኖራል። ዋናው ነገር ምንድን ነው፤ የዛሬ 30 ዓመት ከነዛ ሁሉ ጓዶች ጋር ስንጀምር የፍትሕ፤ የብሔራዊ ነፃነት፤ የዴሞክራሲ ሁኔታ ነበር። አሁን ያ ሁሉ ሰው ከተሰዋ በኋላ እኛም ጓዶች በተሰዉ ቁጥር ትግሉን፤ "ዓርማውን እንስተናል፤ ትግሉን እንቀጥላለን!" ብለን ከፎከርን በኋላ ሁኔታዎች የባሱ ናቸው። በፍትሕ የሄድን እንደሆነ የባሱ ናቸው። ዛሬ በሀገራችን ድህነት ምን ያህል መናጢ እና የሰፋ እንደሆነ ግልፅ ነው። በአንድ በኩል በነፃ ገበያ ግርግር የከበሩ ጥቂት ሰዎች አሉ። በዚሁ በነፃ ገበያ ደግሞ ሚሊዮኖች በየቀኑ ቁጥራቸው እየጨመረ የሚሄድ አስከፊ የሆነ ማጣትና መራቆት ውስጥ እየወደቁ፤ ፍትሕ የሚባለው ነገር ሽታው የጠፋበት ሁኔታ ነው። ከዛሬ 30 ዓመት ወዲህ ዛሬ ሀገራችን ይበልጥ ድሃ ነች። ህዝባችን ይበልጥ ይበልጥ ድሃና ጎስቋላ ነው። እና ይህንን ሁኔታ ስታይና ይህን ይህን ማድረግ አለብን በማለትና መታገል ሲቻል ማቋረጥ የነዛን ሁሉ ጓዶች ሰማዕትነት መጉዳት ነው። ሁለተኛ አሁን የሚሰቃየውን ህዝብ ጅብ እንዲበላው ትቶ እንደመሄድ ስለሚቆጠር፤ በእውነቱ እኛ ምርጫ አለን ምንም ጥርጥር የለውም። በፈለግን ጊዜ ልናቋርጥ እንችላለን። ግን ምርጫ የሌለው ትግሉን መቀጠል ያለበት ህዝብ አለ። ከኛ ይበልጥ የሚሰዋው፤ የሚሞተው፤ የሚጎሳቆለው፤ … የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ላለፉት 30 ዓመታት እኛ ታግለን እንጂ ምንም የሆነው ነገር የለም። ፈቅደን ነው ደግሞ። ስለዚህ ለህዝባችን እናስባለን ካልን እንደውም የኔ 30 ዓመት መታገል ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ከዕለት ዕለት የሚያሽቆለቁል ኑሮ ውስጥ መኖሩ ነው የሚያሳስበኝ። ይህ ማለት ደግሞ ተስፋ መቁረጥ የለም ማለት አይደለም። አንዳንዴ ጨርሶ ነገሮች እንደው ጭልምልም የሚሉበት ወቅት አለ። ባኳያውም እንደ አሁኑ እንደ ባለፈው አንድ ዓመት እንደሆነው ነገሮች በጣም ጥሩ ሆነው መጭው ጊዜ ብሩህ ሆኖ የሚታይበት ሁኔታ አለ። እናም ጭልም ባለበት ጊዜ ይህንን ህዝብ፤ ይህንን ትግል እንዴት ትቼ እሄዳለሁ - በዚህ ጊዜ? ትላለህ፤ ብሩህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ድል ተቃርቧል ለምን ትቼ እሄዳለሁ? ትላለህ። እንዲህ እያለ ነው 30 ዓመት የሞላነው ማለቱ ነው።

**ማለዳ፦** *ያለፉትን የትግል ዘመናትዎን መለስ ብለው ሲያስቡ በተለይ 'ያንን ማድረጌ ትክክል ነበር' ብለው የሚኮሩበት፤ በአኳያውም 'ያንን ማድረግ አልነበረብኝም!' ብለው የሚጸጸቱበት ነገር ካለ ቢያብራሩልን?*

**ዶ/ር ነገደ፦** በመጀመሪያ ነገር ሰው ሁሉ የሚጠብቀን ሂስ አድርጉ፤ ሲለን ከደርግ ጋር ሰርታችኋል፤ ምናምን የሚለውን ነገር ነው። በዛን ጊዜ ልክ አሁን በምርጫው እንደምታገለው ብዙ ኃላፊነትና፤ በአቋም ደረጃ፤ በጽሑፍ ደረጃ፤ በመኢሶን ክርክር በተካሄደው ሸንጎ ገትሬ

(ወደ ፴፬ ዞሯል)


## (ከገፅ ፴፱ የዞረ)

ከደርግ ጋር ከራቲካል ሰፖርት በሚለው አቋም መሥራት አለብን በሚል ሽንጤን ገትሬ የምታገል ሰው ነበርኩ። ልክ አሁን በምርጫው ጉዳይ እንደሚካሄደው ክርክር ማለቱ ነው። እናም ከደርግ ጋር እንደመሥራታችን (አንድ ለሃያ ወር የሚሆን) ምንም የሚቆጨን ነገር የለም። ነገር ግን ከደርግ በተለየንበት ጊዜ በቂ ዝግጅት አልተደረገም። ትልቁ ጉዳት ያመጣው ነገር በጊዜው አለመውጣት ነበር። በነበረው ሁኔታ ማለትም ትግሉን እስካራመደ ድረስ ከደርግ ጋር አብረን እንሠራለን፤ ትግሉን የሚያደናቅፍ በሆነበት ጊዜ ደግሞ የተፈለገ መስዋዕትነት ከፍለን ከደርግ እንለያለን የሚል አቋም ነው ከመጀመሪያው ስንገባ ጀምሮ የነበረን። ትግሉን ያደናቅፋል የሚል ደረጃ ላይ ስንደርስ ሚኒስቴር የነበረው፣ ትላልቅ ሹም የነበረው በሙሉ እንዳለ ለቆ አንደር ግራውንድ እንዲገባ አደረግን። እናም ያ ውሳኔ በደንብ በተደራጀ መልክ ቢሆን ኖሮ ብዙ ከጥፋቶች እንድን ነበር። የሚቆጨኝም ያ ነው፤ ማለት ከደርግ መለየታችን ሳይሆን በይበልጥ ሳንደራጅ በተዘጋጀ መልክ ባለመለየታችን። እሱ ነው የሚቆጨን እስካሁን። ሌላ የሚቆጨኝ ነገር የለም።

__*ማለዳ*__፦ *ስለኢትዮጵያና ስለህዝቧ ያለዎት ራዕይ ምንድን ነው?*

__ዶ/ር ነገደ__፦ ወደ አዲስ ክፍለ ዘመን እየገባን ነው። መቼም እኔ ያለፈውን ክፍለ ዘመን ግማሹን ኑሬበታለሁ፣ ግማሹን አልኖርኩበትም። ያለፈው ክፍለ ዘመን የባከነ ብኩን ክፍለ ዘመን ነው፤ ፊት ኃይል የሆነ የሚል ነው ያለኝ አመለካከት። ምክንያቱም ዘመኑን ስንጀምር ዴሞክራሲ፣ ሰላም፣ ብልፅግና እያሉ የተነሱ ኃይሎች ነበሩ። ምሁራኖች። እኛ እንደምንታገለው እነገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ እነአፍወርቅ ገብረየሱስ፣ ... ሌሎችም ብዙ ምሁራን ነበሩ። ራሳቸው ኃይለሥላሴ ተፈሪ መኮንን ተብለው በመጣትነታቸው ይህንን ያራምዱ ነበር። እስከ ክፍለ ዘመኑ መጨረሻ ስንት መስዋዕትነት ተከፍሎ ስንት ሃሳቦች ተንሸራሸረው አሁንም እዛው ላይ ነን። ማለትም አሁንም ፍትሕ እንላለን፣ ዴሞክራሲ እንላለን፣ ሰላም እንላለን። እነዚህ ሦስቱም አልተገኙም። ትልቁ ስጋቱ አዲሱን ክፍለ ዘመን እንደዛው ጀምረን እንደዛው እንዳንጨርስ ... አለ አይደለም ... እስከዛ ግን አገሪቱም ትጠፋለች። እንደዚህ መቀጠል አትችልም። ይህንን እንዳንጀምር፣ እስከአሁን ሰላምን፣ ዲሞክራሲን፣ ለውጥን እርስ በርስ እያጣፋን ነው የመጣነው። በእውነት! ባጠቃላይ ሳየው አሁንም ቀርቶናል። እኔ ስለቀጣዩ ምርጫ አይደለም፣ ስለቀጣዩ ክፍለ ዘመን ነው ራዕይ ያለኝ። ይሄን ምርጫ፣ እና እንቅስቃሴ አዲሱን ክፍለ ዘመን ሦስቱንም ማለትም ሰላምን፣ ፍትህን፣ ዲሞክራሲን ለውጥን እነዚህን እሴቶች ሳናምታታ እያስተጋገዝን ሀገራችንን ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ የምናደርግበት ሂደት እንድንጀምር ነው ትልቁ ራዕዬ።

ይህን ለማድረግ ደግሞ ይቻላል ነው የምለው። ኦፕቲሚስቲክ ነኝ። የምርጫው የሽግግር ዘመን ሁለት ዓመት ነው ተብሏል። በሃቅ የሚደረገው ምርጫ ነፃና በዴሞክራቲክ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚደረገው ምርጫ ከተሳካልን ክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ነው ማለት ነው። ማለትም በእኛ ሁለት ሺህ። እና ያን ጊዜ አዲሱን ክፍለ ዘመን በአዲስ መልክ አዲስ ኅብረተሰብ ለመገንባት የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ ተቃቅፈው በወንድማማችነት የኢትዮጵያ ክፍለ ዘመን እንዲባል ነው የምፈልገው። አሜሪካኖችም "ፕሮጀክት ፎር ኤ ኒው አሜሪካን ሴንቸሪ" የሚል አንድ ፕሮጀክት አይታችኋል፤ ... ከሦስት ዓመት ክፍለ ዘመኑ ከመቀየሩ በፊት እኛ እንደዛ ይዘን መነሳት አለብን። ለኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ክፍለ ዘመን እንዲሆን የሚያንሰን ነገር የለም። ከህዝብ ብዛት፣ ከዓለም ካሉት አስር ታላላቅ ሀገሮች አንዱ ነን፣ ከሀብትም ሀብት አለን። አስተዋይና ታታሪ የሆነ ህዝብ አለን። አዳዲስ ሃሳቦችን በኃይል የመቀበል ችሎታ ያለው ህዝብ አለን። የረዥምም ጊዜ ስልጣኔ ያለው፣ ጨዋ ባህል ያለው ህዝብ ነው ያለን። እሴቶቹ በሙሉ ስላሉን አሁን ይህንን አዲሱን ክፍለ ዘመን በደንብ አድርገን በአዲስ ተስፋ ለመጀመር እንችላለን። ሽግግር ስንል ሁለት ሺህ ዓመት ላይ እንደርሳለን። ያን ጊዜ አዲስ ምርጫ እናደርጋለን የሚል ነው ተስፋዬ።




__*ማለዳ*__፦ *በመጨረሻም እስኪ ስለቤተሰብዎ ያጫውቱን - ስለትዳርዎና ስለልጆችዎ ...*

__ዶ/ር ነገደ__፦ መልካም! ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ። ከባለቤቴም ጋር አንድ ላይ ነው የምንኖረው። ከባለቤቴ ጋር ወደ 30 ዓመት ግድም ሆኖናል። ድሮ የአውሮፓ ማኅበር ታጋይ ነበረች። ከመኢሶን አንደር ግራውንድ በኋላ ተጋብተን እስከ አሁን አብረን አለን። ልጆቼም ተማሪዎች ናቸው።

__*ማለዳ*__፦ *ዶ/ር ነገደ ጎበዜ የመኢሶን ሊቀመንበርና የሕብረት አመራር አመሰግናለሁ!*

__ዶ/ር ነገደ__፦ እኔም አመሰግናለሁ! ■